"ሙባረክን ያያችሁ ተቀጡ!"

የካቲት 2003 ዓ. ም.
ከነቃጥበብ፣ ለንደን

እማተ ገሞራ ተንጦ ተንጦ፣
መፈንዳት ሲጀምር መሬቱን ገልብጦ፣
ተራራ፣ ኮረብታ፣ ገደል አነዋውጦ፣
መግጠሚያ የለውም በምን ይመረጋል?
ነዲድ እየተፋ ዶግ አመድ ያደርጋል።
የሕዝቡም እሮሮ ተንጦ ተንጦ፣
መፈንዳት ሲጀምር ሥርዓት አንቀጥቅጦ፣
በምን ይገደባል ነገር ተለዋውጦ።

የሕዝብ ከባድ አመጽ፣ በሕዝብ የታቀፈ፣
መፈንዳት ሲጀምር እየተጧጧፈ፣
ማን ይገድበዋል ወሰኑን ካለፈ?
ፖሊስ ደህንነቱ፣ ሠራዊት ቢሰለፍ፣
የመሣሪያው ዓይነት በያይነቱ ቢጎርፍ፣
የሰዓት እላፊ ደጋግሞ ቢለፈፍ፣
እንደግብፅ አብዮት መሬት ቁሊጥ ስትሆን፣
አልተኩስም ካለ ከሕዝብ በመወገን፣
ከንቱ መታከት ነው የሚሆነው ሲሆን!

"በፊት ነበር እንጅ መጥኖ መደቆስ፣
ሁዋላ ምን ያደርጋል ወጭት ጥዶ ማልቀስ?"
እንደሚለው ተረት ለሁሉም እንዳይተርፍ፣
ማነው ባለሳምንት? ከዚህ ትምህርት ያግኝ፣ ጊዜው ሳይል
የሙባረክ ጭንቀት መግለጫ ማብዛቱ፣
"እኔን ያየህ ተማር" ያሰኛል በእውነቱ።

አምባ-ገነን ሁሉ በያለበት ያለ፣
በዴሞክራሲ ስም ህዝብን ያታለለ፣
ከግብፅ ትንሽ ትምህርት ቢቀስም ምን አለ?
ከግብፅ የሕዝብ አመፅ አምባ-ገነን ይማር፣
ማቄን ጨርቄን የለም በእምቢታ ሲወጠር።

"ዘጠና ዘጠኙ መራጭ ደግፎኛል፣
ስም ማጥፋት ነው እንጅ ሕዝቡ ይወደኛል፣"
የሚባለው ተረት የማታለያው ቃል፣
እስቲ ሰልፍ ይፈቀድ፣ እውነቱ ይለያል!
ባለፈውም ቢሆን ባደባባይ ታይቷል፣

ሕዝብ እንደታፈነ እስከመች ይኖራል?
አመፅ መፈንዳቱ ከሩቁ ይሸታል።

　　የሕዝብን ጥያቄ ብሶቱን ተረድተው፣
　　መፍትሄ የሚሹ በጧት ተሰናድተው፣
　　የዚህ ዓይነቶቹ፣ የሕዝብ መሪዎች፣ የታደሉ ናቸው፣
　　ለማንም ለምንም አይተርፍም ጠሳቸው።

እንዳይነድ እርጥቡ በደረቁ አበሣ፣
የተኛ አምባ-ገነን፣ ከእንቅልፉ ይነሳ፣
ከመድረሱ በፊት አመፅ እያገሣ።

　　"በሡራዊት ብዛት ንጉሥ እንደማይድን፣"
　　ዳዊት አስተምሯል በወዳኛው ዘመን፣
　　እኛም አይተነዋል ደጋግመን ደጋግመን፣
　　የሃይሌ፣ የመንጌ ምድር ቁሊጥ ስትሆን።

"ሙት ይዞ ይሞታል' እንዳይሆን ነገሩ፣
ህሊና ካላችሁ በጊዜ ምከሩ።
ሰው ብሶቱ በዝቶ ሞትን ከመረጠ፣
ሌላ ምን ይመጣል ከዚህ የበለጠ?

　　የእኛ አምባ-ገነኖች ከታሪክ ተማሩ፣
　　የነገን አታውቁም የዛሬን ቀን ፍሩ፣
　　ምንም አያዋጣም፣ ሕዝብን መሸንገሉ፣ መላ መደርደሩ።